# ነገር ሳይበላሺ ቶሎ ቢደርስልኝ

**ሰመረ አለሙ**

ይህ ጽሁፍ የቃላት ዉበት የሚያስፈልገዉ ሳይሆን ጊዜ የማይሰጥ ጉዳይ በመሆኑ ኢትዮጵያዉያን እንዲመክሩበት ታስቦ የተላከ በመሆኑ ይህን ነገር አንባቢ ትኩረት ሰጥቶ እንዲወያይበት ለመንግስት ቅርበት ያላቸዉም ይህን ታክኮ የችግሩን አሳሳቢነት ለአመራሩ እንዲያቀርቡ የታሰበ አስቸኳይ መልእክት ነዉ።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ከደረሰችባቸዉ ታላላቅ ስምምነቶች መካከል ዋናዉ በአስተዋዩ መሪያችን በዳግማዊ አጼ ምንሊክ አማካይነት በደም ማህተም አደዋ ላይ ማስተካከያ የተደረገበት የዉጫሌዉ ዉል ሲሆን ቀሪዉ ግን እስከ አሁን ህልዉናችን ላይ ተጋርጦ ለተከታዩ ትዉልድ መፍትሄ እንዲፈልግለት የተተወ  የሀገር እዳ ሁኖ ትዉልድ ሲቀባበለዉ እዚህ ደርሷል።

ኢትዮጵያ ስምምነት ተበላሺቶባት ዋጋ ከከፈለችባቸዉ ጉዳዮች መሀከል

1. የወደፊቱ ከግምት ሳይገባ አገር የሚያህል ቦታ በኤምባሲዎች መያዙ

2. ኤርትራ ከእናት አገሯ ተገንጥላ ስትሄድ የትግሬዎች መንግስት ያደረገዉ አሳፋሪ ስምምነትና

3. አሁንም በትግሬዎች መንግስት ስምምነት ለሻቢያ የተሰጠዉ የትግሬዎች መሬትና የባህር በራችን ዋና ዋና ጉዳይ ሁኖ በቅርቡ ደግሞ  የኢትዮጵያ ተስፋ የሆነዉ አባይን **ኢትዮጵያዊ** ወይም **ግብጻዊ** ለማድረግ የሚደረገዉ ፍትጊያ ነዉ።

ከግብጽ በኩል የግብጽ ህዝብ፤ ምሁራን፤ ጋዜጦች የሞት የሺረት ትግል አድርገዉ ይህንን ጉዳይ ወጥረዉ ሲይዙ በኢትዮጵያ በኩል የዶ/ር አብይ መንግስት አያገባችሁም በሚል መልኩ ጉዳዩን ከዜጎች ሳይመክር በዝግ ስብሰባ ነገሩን ለመቋጨት የዉጭ ጉዳይ ሚኒስተሩን ወደ ልእለ ሀያሉ አገር አሜሪካ ልኳል። በዚህ ጉዳይ አልሲሲ በተለያዩ የአለም ክፍሎች ተጉዞ፤ አረብን አሳምጾ፤ አሜሪካንን ለምኖ፤ ከምሁራንና ከጦር ሰዎች መክሮ፤ትላልቅ የገንዘብ ተቋማትን ከጎኑ ሲያደርግ በተራዉ የኢትዮጵያ መንግስት የባህር በሩን አስረክቦ፤ መሬቷን በሀይል የቀሙትን ሀይሎች በቀይ ምንጣፍ በትልቅ ክብር ያስተናግዳል።

እንደ አባይ ያለ ተስፋ የጣልንበት ሀብት ሰለቸኝ ደከመኝ  የሚባልበት ሳይሆን እስከ መጨረሻዉ የህይወት እንጥፍጣፊ ተጉዞ፤ ሐይልን አሰባስቦ፤ ዜጋን አስተባብሮ የሚዘመትበት ታላቅ ብሄራዊ ጉዳያችን ሁኖ ሳለ አመራሩ እንደ ግብጾች ነገሩ ሳያሳስበዉ ተዝናንቶ ጉዳዩን አካባቢዉ ላሉ ሰዎች ትቶ የተዘናጋ ይመስላል። ዶ/ር አብይ እድገታቸዉ ኢህአደግ ቤት ሁኖ እንደ ቀድሞ የትግል ጓዶቻቸዉ የሀገር ጥቅም ብዙም ሳያሳስባቸዉ ቀርቶ ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት ስለ ነገሩ ብዙም ሲጨነቁበት ከምሁራንም ጋር ሲመክሩበት አይታዩም ። ቀደም ባለዉ ጊዜ ኮለኔል መንግስቱ መሳሪያ ማምረት ከጀመሩ በኋላ በወንዜ ላይ የሚያዝበት ማነዉ? ብለዉ በሀገር ፍቅር ስሜት የተናገሩት ዛሬ ላይ ከብዙ ክፉ ስራቸዉ በላይ ጎልቶ ይታወሳል። መለስ ዜናዊም ቢሆን ምንም እንኳን የችግሮች ሁሉ ጥንስስ የክፋትና የጥፋት ምንጭ ቢሆንም ግብጾች ጦርነት ካሰቡ ይሞክሩት ብሎ በ CNN መግለጫ መስጠቱን ማዉሳት ለዶ/ር አብይ ድፍረት ይሰጥ ይሆናል ብለን ደግመነዋል  ። ለወትሮዉ ወታደር ለሀገሩ እራሱን አሳልፎ የሰጠ በባንድራዉ የማለ ነበር ሀገርን አደጋ ሲገጥማት ከምንም በላይ ቅድሚያ  ሰጥቶ ለሀገሩ ሟችም ነበር።

ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ፤ መሬት እየጠበበ፤ ህዝቡ በደናቁርትና በብሄር ፖለቲከኞች እየታመሰ፤ የህዝብ ኑሮ ከእለት ወደእለት እየተመሰቃቀለ፤ የኑሮ ዉድነት እየናረ ያንን የሚያካክስ ምንም ነገር በጠፋበት ጊዜ ተስፋችን ሁኖ የተገኘዉ አባይ ቢሆንም እስከ አሁን በታየዉ ናሙና ኢትዮጵያ ከድርድሩ የሚገባትን ታገኛለች ብሎ ብዙም መጠበቅ ያለብን አይመስልም። ባለፈዉ የግብጽን ማስፈራራት አስመልክቶ በቂ ማብራሪያ የተሰጠ ቢሆንም የግብጽ ማናፋት ኢትዮጵያ ላይ ቅንጣት ያህል ጫና ማሳደር አለመቻሉን የአለም አቀፍ የወታደራዊ ተቋሞች የሰጡትን ትንተና አያይዘን አቅርበንም ነበር።መሪዎቻችን ጥንካሬ ቢኖራቸዉ በዲፕሎማሲዉ ሜዳ ዘዋሪ( ጌም ቼንጀር)  ሁነዉ ኢትዮጵያን ተለማኝ እንጂ ለማኝ አለማድረግ ይችሉ ነበር። በእዉነቱ ሞትን የምንኮንንበት ጊዜ አሁን ነዉ አክሊሉ ሐብተወልድ፤ይልማ ዴሬሳ፤ከተማ ይፍሩ ከየት ይገኙ ዛሬ?

ዶር አብይ እንደ መለስ ዘራዊ በእዉቀት የታጠቁ ሰዎች የሚመቿቸዉ አይመስልም በየቦታዉ አብረዋቸዉ የሚጓዙትም የእሳቸዉ አድናቂዎችና ተማሪዎች ወይም ደግሞ የደነዘዙ የቀድሞ የነገድ ድርጅት መሪዎች ናቸዉ። እነዚህ ግለሰቦች አገሪቱን  ዘመን ተሻጋሪ የሆን የኢኮኖሚ ፍልስፍና ቀምረዉ መጭዉን ዘመን በእዉቀት መነጽር አሻግረዉ ማየት የማይችሉ ከመሆናቸዉም በላይ ቅኝታቸዉ በስልሳዎቹ ፍልስፍና ቆሞ የቀረ ከዘመኑ ጋር መለወጥ የማይችል በመሆኑ እነዚህ አጃባዎቻቸዉ በዚህ በከፍተኛ ፍጥነት ተለዋዋጭ በሆነዉ አለም  ለሀገር የሚበጅ ነገር ያመጣሉ ብሎ መገመት በእጅጉ አስቸጋሪ ይሆናል።

አባይ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ሲጀመር የኢትዮጵያን ልጆች አንሰላስሎ ከመያዝ ባሻገር አንደነታችንም ለማጠናከር ተፈጥሯዊ ተልእኮዉን በመወጣት  ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ከማድረጉ ባሻገር ወደ ቀድሞ ክብሯ እንደሚመልሳትም ጥርጥር የለዉም። ይህ ድህነትና የዘር ልክፍት ያጋጨዉን ህዝባችንን ትልቅ ተስፋ ይሰጠዋል፤ ኑሮዉንም ያጣጥማል፤ የኢኮኖሚ ሀይሉንም በእጅጉ

ያሳድገዋል። በእርግጥ የጎጃም ህዝብ ወንድሞቹ ከየቦታዉ በኦሮሞና በትግሬ ጽንፈኞች ቢታደኑበትም ወንድሞቹ ኢትዮጵያዉያን የዚህ በረከት ተኳዳሺ እንደማያደርጋቸዉ በሙሉ ልብ መናገር ያስችላል። ግብጾች ባለፈዉ እንደጠቀስነዉ ከ11 ክፍለ ዘመን ጀምሮ ፖሊሲያቸዉ **እነዚህ አበሾች ሰላም ካገኙ በአባይ ላይ የበላይነት ይኖራቸዋል በሚል የዉጭ ፖሊሲያቸዉ** የእናት ጡት ነካሺ የሆኑ ድርጅቶችን ኢህአፓ/ሻቢያ/ተፒለፈ/አነግን ከማስተናገዳቸዉም በላይ በሙርሲ ዘመነ መንግስት ሾልኮ በወጣዉ በሚንስተሮች ስብሰባ ላይ የኦሮሞን ድርጅቶች በገፍ እንረዳለን ያሉትን ባልታሰበ መልኩ የኢትዮጵያ አምላክ እኛዉ ዘንድ አድርሶት አይተናል ሰምተናልም። ሙርሲም በኢትዮጵያ በመዶለቱ አሚሚቱ ሳያምር ቀረ በዛ ሳያበቃ መለስ ዜናዊም ብዙም ሳይቆይ ከማቀዝቀዣ ወደ ማቀዝቀዣ ሲገለባበጥ ወደማይመለስበት ሄደ። መቼም ቋሚ ከዚህ ይማራል ብለን እንገምታለን።

ግብጾች  የአባይ ወንዝ ድርሻቸዉ ከበቂ በላይ እንደሆነ ያዉቃሉ ከሚጠቀሙበት በላይ በብክነት የሚያጠፉትም ይበዛል እንደዉም በአንድ ወቅት አሳልፈዉ ለእስራኤል ሊሸጡት ሁሉ በድርድር ላይ ነበሩ።  ጭንቀታቸዉ ኢትዮጵያ ከበለገጸገች አንድ ከሆነች በወታደራዊ አቅሟ ከጠነከረች አስፈራርተን የምናገኘዉ ይቀርብናል ከሚል እሳቤ የመነጨ ነዉ። ግብጾች እስከዛሬ አባይን በተመለከተ ኢትዮጵያ ጋር ስምምነት አድርገዉ አያዉቁም። ቀደም ያለዉ ስምምነት በግብጽና በቅኝ ገዥዋ እንግሊዝ ነዉ (1928) ይህን ስምምነት ኢትዮጵያ የማክበር የህግም ሆነ የታሪክ ግዴታ የለባትም። ሁለት ሀገሮች በሌላ ሀገር ጉዳይ ለመወሰን የሚያበቃ የህግ አመንክዮ የለም። ግብጾች ሰዊዝ ካናልን በእንግሊዞች ይዞታ ስር ቢሆንም ስምምነቱን በመጣስ እንደወረሱት ሁሉ ኢትዮጵያም አባይን በፈለገችዉ መንገድ የመጠቀም ሙሉ መብቷ ነዉ የሚያግዳትም የህግ ስምምነት አይኖርም። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ እንደ ግብጽ ኡጋንዳ ኬንያ ሱዳን የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ባለመሆኗ የተጠቀሰዉ ስምምነት በፍጹም አይመለከታትም የኢትዮጵያ መንግስትም ያንን ስምምነት ስምምነት ብሎ ሊጠራዉም አይገባም። ሌላዉ ስምምነት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ትርጉሙ የተለያየ በመሆኑ የተዛባ ስምምነት ስምምነት ተብሎ ሊወሰድ ባለመቻሉ እሱም ላይ ኢትዮጵያ የበላይነትን ይዛለች።

ይህንን ከላይ እንዳመላከትነዉ ሁኖ ኢትዮጵያና ግብጽ አባይን አስመልክቶ ስምምነት ላይ የሚደርሱት ለመጀመሪያ ጊዜ ይሆናል ማለት ነዉ።ግብጾች ማንኛዉም ስምምነት ያስደስታቸዋል አባይን ለመጠቀም የህግ ማእቀፍ ይሰጣቸዋል። ግድቡን በ4 አመት እሞላዋለሁ ብላ ኢትዮጵያ ጠንክራ ብትቀርብ በደስታ ይቀበሉት ነበር የነሱ ሃሳብ በብዙ ጥያቄዎች ኢትዮጵያን ለጥጦ አሳክሮ ግማሺ መንገድ ተጉዞ ስምምነት ለማስፈረም ነበር ይህንንም አሳክተዉታል። ከዉጭ ጉዳይ መግለጫ እንደሰማነዉ <u>**የተፋሰስ አገሮችን ታሳቢ ያደረገ፤ከግምት በማስገባት፤**</u> **ወዘተረፈ** የሚለዉ ክፍተት ያለበት የህግ ቋንቋ ተወግዶ ጥርት ባለ ቋንቋ ኢትዮጵያ ዳግም ስምምነቱን ጊዜ ወስዳ ልታጤነዉ ይገባታል። ግብጽና ዶናልድ ትራምፕ ስለፈለጉ ስምምነት ያልሆነ ስምምነት መፈረም ኢትዮጵያንና መጭዉን ትዉልድ አቀጭጮ ኢትዮጵያ ዘወትር ለማኝ ሁና እንድትኖር የሚያደርግ ስምምነት ነዉ። አማራ፤ኦሮሞ፤ደቡብ፤ቋንቋ፤ማንነት....በሚለዉ ተቧድኖ ህዝቡ ከሚተላለቅ በዛች ምድር የተፈጠረ ዜጋ ሁሉ  እንደ ንብ ተቀስቅሶ አመራሩንም ሆነ ግብጽን እጅ ጠምዝዞ  ለኢትዮጵያ በሚበጅ መልኩ ስምምነት ላይ መደረስ አለበት። ስምምነቱም ከመፈረሙ በፊት ህዝባዊ ዉይይት ሊደረግበት ይገባል የዉሃዉ ባለቤት ሳዉዝ አፍሪካ እግር ላይ ወድቆ አሸማግሉኝ ብሎ ከመሸብረክ ዜጎችን ይዞ አስፈላጊም ከሆነ ሰንደቁን ይዞ ለህዝብ ምሳሌ ሁኖ የመሪነት ብቃቱን ማሳየት አለበት።

ግብጾች <u>ክርሲቲያኖች፤እስላሞች፤አይሁዳዉያን</u> የግብጽን ጥቅም በተመለከተ አንገታቸዉን ሲሰጡ እነ አህመዲን ጀበል አቡበከር በየፓልቶክ ክፍል ከወገናቸዉ ይልቅ ለግብጾች ስስ ልብ እንዳላቸዉ በየጊዜዉ በሚያስተላልፉት  መልእክት ታዝበናል። ጁዋር መሀመድም እንዲሁ ቀለቡን ከግብጽ እንደሚሰፈርለት እናዉቃለን። አሜሪካም ሆነ የአለም ባንክ በዚህ ፕሮጀክት ስላልረዱን ጉዳዩ ስለማያገባቸዉ ቀደም ሲልም እንዲሳተፉበት መደረጉ አግባብ ካለመሆኑም በላይ አንድ ጠንካራ መንግስት የዉጭን ጣልቃ ገብነት በእጇ ሊቃወም በተገባ ነበር ታድያ ምን ይሰራል ሀገር ወዳድነትን ፓትሮይቲዝም ከዉስጥ ከሌለ በትምህርት ወይም በምክር ሊዋሀድ ባለማቻሉ ከላይ በግድ የተቀመጡ መሪዎች ኢትዮጵያን ላለፉት 50 አመት ወዴት እንደወሰዷት ቋሚ ምስክር በመሆኑ ዝርዝሩ አስፈላጊ አይሆንም።

ዶር አብይ አያገባችሁም የምንሰጣችሁን ተቀበሉ የሚሉት ዝንባሌ ትላንት ድርጅታቸዉ ኢትዮጵያን በተለያየ አለም አቀፍ ድርድሮች ደካማና ለማኝ፤ተጠቂ፤ተሸናፊ አድርጎ  አሳልፏታል  በአንድ ወቅት ስለ ሻቢያ ጉዳይ ከኢትዮጵያም የተወከሉት ሻቢያኖች ከኤርትራም የተወከሉት ሻቢያኖች ሁነዉ በድርድር ጠረቤዛዉ ላይ ያላግጡብን ነበር እንግዲህ ዶክተር አብይ ዛሬም ይህንን አሳፋሪ ክስተት ይደግሙታል ብለን አንጠብቅም።በተራቸዉ  ከዚህ የዉርደት ታሪክ  ወጣ ብለዉ አድዋን በአባይ እንዲደግሙ በጥብቅ እናሳስባለን። ዶ/ር አብይ ወምበራቸዉ ላይ ለዘላለም አይቆዩም አሁን የሚያደርጉት ጠንካራም ሆነ ደካማ ዉሳኔ እሳቸዉ ካለፉ በኋላም በታሪክ መዝገብ ሰፍሮ ኢትዮጵያ እስካለች ጊዜ ድረስ ለዘላለም ይኖራል። እንግዲህ ዶ/ር አብይ በምን ሊታወሱ እንደፈለጉ የሚያዉቁት እሳቸዉ ናቸዉ በህይወት በመቆየታቸዉ የኮለኔል መንግስቱንም የሐይለ ማርያምንም፤ የመለሰ ዜናዊንም ዘመን ተመልከተዋል ህዝቡም እንዴት እንደሚያስታዉሳቸዉ ጠንቅቀዉ ያዉቃሉ።

ዛሬ ግብጾች በሚፈልጉት መንገድ ከተፈረመ ነገ አንድ እግረ በቆሎ አምርቶ ገበሬ እንዳይበላ ግብጾች ባላቸዉ ሳተላይተ መረጃ እየሰበሰቡ ስምምነት ጥሳችኋል እያሉ ህዝባችንን ጤና ስለሚነሱት ማንኛዉም ስምምነት እነሱ በሚፈልጉት ሳይሆን እኛ በምንፈልገዉ ከማድረግ የሚያግዳቸዉ  ምድራዊ ሐይል አይኖርም። በህይወት ባይኖርም ጀግንነትን ከሙጋቤ መዋስም ይቻላል። እዚህ ላይ ብዙ ወገን ግብጾች የዉሀ ችግር ያለባቸዉ ይመስለዋል አይለም በጣም ግዙፍ የሆነ የምድር የዉሀ ክምችት አላቸዉ

ያንንም አዉጥቶ ለመጠቀም አቅም አላቸዉ የነሱ ትልቁ ችግር ግን ኢትዮጵያ ዉሃዉን ለልማት እንዳትጠቀም  ቢቻል በወታደር ካልተቻለም በህግ ማእቀፍ ቸንክሮ መቀመጥ ስለሆነ ማንኛዉም ዜጋ ለዚህ ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ ማፈናቀሉና መገዳደሉን ለኋላ አቆይቶ ለዚህ ጊዜ ለማይሰጥ ጉዳይ ርብርብ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ እንላለን።

ስምምነቱ አሁንም ይከለስ በዚህ ጉዳይ መሰልቸት ሊኖር አይገባም እንደሚገባኝ ግብጾች የሚፈልጉትን አግኝተዋል የዉሀ ችግርም የለባቸዉም፤ ለድርቅ ጊዜ የሚሆናቸዉን ዉሃም የማከማቸት አቅም አላቸዉ ዋናዉ ፍላጎታቸዉ ኢትዮጵያ አባይን ተጠቅማ በተሻለ የኢኮኖሚ ደረጃ እንዳትደርስ ማድረግ ነዉ ከላይ እንደተጠቀሰዉ ይህ የቆየ የግብጽ የአባይ ፖሊሲም ነዉ።

ስምምነቱ ዳግም በኢትዮጵያ ሊቃዉንት ተከልሶ የስዩም መስፍን አይነት ስምምነት ሳይሆን ኢትዮጵያን ዘመን በተሻገረ መልኩ እንዲጠቀም እንዲደረግ ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች ከሀገር ቤትና ከሀገር ዉጭ መሳተፋቸዉ አማራጭ የሌለዉ ምርጫ በመሆኑ ዶ/ር አብይ አዲስ አበባም ሆነ ዋሺንግተን የኢትዮጵያን ልሂቃንን አሰባስበዉ በእዉቀትና በታሪክ ታግዘዉ ከታች ሳይሆን ከላይ ሁነዉ ስምምነት ላይ እንዲደርሱ በኢትዮጵያ ስም እንማጸናለን በእኔ በኩል ለጊዜዉ ስማቸዉ የታወሰኝ ፕሮፌሰር ሐይሌ ላሬቦ፤ዶ/ር አክሎግ ቢራራ፤ ዶ/ር በፍቃዱ በቀለ፤ዶ/ር ደረጀ ዘለቀ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ፤አቶ ተክሌ የሻዉ፤ዶ/ር አበባ ፈቃደ፤ኮለኔል ጎሹ ወልዴ፤ኢነጂነር ይልቃል፤ዶ/ር ያእቆብ ሐ/ማርያም፤አቶ ጌታቸዉ ረዳ (ኢትዮ ሰማይ አዘጋጂ)፤ኢንጂነር ዘገይ ከሲያትል፤ እና የበቁ የነቁ ስለሀገራቸዉ ባለመታከት የሚጽፉ፤ እርምት የሚያደርጉ፤ የሚመከሩ አገራቸዉን የሚወዱ ዜጎች ቢካተቱበት ለኢትዮጵያ መጻኢ እድል ወሳኝ በመሆኑ ዜጎች በዚህ ነገር ላይ ርብርብ እንዲያድርጉ ለማሳሳብ ነዉ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

ሰመረ አለሙ semere.alemu@yahoo.com